በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የ6ኛ ክፍል የሒሳብ ሞዴል ፈተና /ግንቦት 2015 ዓ.ም

ትዕዛዝ 1 የሚከተሉትን ጥያቄዎች በጥንቃቄ በማንበብ ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ መስጫ በተዘጋጀው ወረቀት ላይ መልስ ስጡ፡፡ የተሰጠ ሰአት 1:00

1. የ6 እና የ7 ት.ጋ.ብ ----------ነው፡፡
   ሀ. 36 ሐ.42
   ለ. 52 መ.54
2. ታህቱ 16 የሆነ ለ$\frac{5}{4}$ ተመጣጣኝ ክፍልፋይ ---------- ነው፡፡
   ሀ. $\frac{5}{6}$ ሐ.$\frac{10}{16}$
   ለ. $\frac{20}{16}$ መ. $\frac{25}{16}$
3. ከሚከተሉት ቁጥሮች ውስጥ ብቸኛም ተተንታኝም ያልሆነው ቁጥር የቱ ነው?
   ሀ. 2 ሐ.0
   ለ. 3 መ. 1
4. ከሚከተሉት ውስጥ ኢ-አክታሚ የሆነው ክፍልፋይ የቱ ነው
   ሀ. $\frac{30}{5}$ ሐ. $\frac{50}{3}$
   ለ $\frac{3}{50}$ መ. ሀእና ለ መልስ ናቸው
5. 0.5 × $\frac{3}{4}$=----------
   ሀ. $\frac{3}{8}$ ሐ. 0.375
   ለ.$\frac{5}{4}$ መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው
6. በ 48.652 ውስጥ የመቶኛ ቤት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ.8 ሐ. 6
   ለ. 5 መ. 2
7. 301000 በአስር ርቢ ሲገለጽ --------- ነው፡፡
   ሀ.3.01 × 10^5 ሐ. 3.01 × 10^6
   ለ.301 × 10^5 መ.30.1 ×10^5
8. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ ብቸኛ ሙሉ ቁጥር የሆነው የቱ ነው?
   ሀ.94 ሐ.101
   ለ.86 መ.102
9. 2.45 በክፍልፋይ ሲገለጽ --------- ይሆናል፡፡
   ሀ. $\frac{49}{20}$ ሐ. $\frac{245}{10}$
   ለ. $\frac{20}{49}$ መ. መልሱ አልተሰጠም
10. 2490 በብቸኛ ትንትን ሲገለጽ ---------- ይሆናል፡፡
    ሀ. 2^2× 3 × 5 × 83 ሐ. 2×3×5×83
    ለ. 2^2×3^2×5 መ.2^3×3^2 × 5
11. ከሚከተሉት ሙሉ ቁጥሮች ውስጥ ለ 8 ተካፋይ የሆነው የቱ ነው?
    ሀ. 34640 ሐ. 12513
    ለ. 6590 መ. 9363
12. አየለች $\frac{4}{3}$ ኪ.ግ ሙዝ እና $5\frac{2}{3}$ ኪ.ግ ብርቱካን ብትገዛ በአጠቃላይ ስንት ኪ.ግ ፍራፍሬ ገዛች?
    ሀ. 6ኪ.ግ ሐ. 7ኪ.ግ
    ለ.8 ኪ.ግ መ.መልሱ አልተሰጠም

13. $\frac{3}{10} \times 5\frac{1}{8}$= ----------

ሀ.$1\frac{80}{43}$ ሐ. $\frac{15}{80}$

ለ. $1\frac{43}{80}$ መ. $\frac{80}{123}$

14. ሀ ÷ $\frac{2}{5} = \frac{1}{4}$, የ' ሀ ዋጋ ---------- ይሆናል።

ሀ. $\frac{3}{4}$ ሐ $5\frac{1}{4}$

ለ. $\frac{1}{10}$ መ.$\frac{3}{7}$

15. 3ሸ + 10 = 40 , በተለዋዋጩ ቦታ ተተክቶ አረፍተ ነገሩን እውነት የሚያደርግ ቁጥር የቱ ነው?

ሀ. 20 ሐ.15

ለ. 10 መ.30

16. መ - $\frac{6}{5} = \frac{8}{7}$ የ መ ዋጋ ---------- ነው ።

ሀ. $\frac{82}{35}$ ሐ.$\frac{35}{82}$

ለ. $\frac{41}{35}$ መ.$\frac{14}{12}$

17. የ ኢ-ርቱዕ ወደረኝነት ዝምድናን የሚያሳይ ቀመር የትኛው ነው?

ሀ. ቀ= ጠሸ ሐ.ቀ = $\frac{ጠ}{ሸ}$

ለ. $\frac{ዕ}{ለ} = \frac{ሞ}{ሠ}$ መ. መልሱ አልተሰጠም

18. $\frac{1}{2}$ ቀ< 45 , በተለዋዋጩ ቦታ ተተክቶ ያለእኩልነት አረፍተ ነገሩን እውነት የሚያደርገው ----- ነው።

ሀ. ቀ < 90 ሐ.ቀ > 90

ለ. ቀ ≤ 90 መ.ቀ ≥ 90

19. አንድ ሞተር ሳይክል በአንድ ሰአት 45ኪ..ሜ ቢጓዝል ፤በተመሳሳይ ፍጥነት ለ 5 ሰአት ቢጓዝ ምን ያህል ኪ..ሜ ይሸፍናል?

ሀ. 200 ኪ..ሜ ሐ.225 ኪ..ሜ

ለ. 150 ኪ..ሜ መ.መልሱ አልተሰጠም

20. ባለ ብዙ መቀመጫ መሰረት እና ጎኖቹ ጎነ-ሶስት ምስል የሆነ ጠጣር ምስል -------- ይባላል።

ሀ. ፒራሚድ ሐ. ኩብ

ለ. ሲሊንደር መ.ሬክታንጉላር ፕሪዝም

21. -------- ጎነ-ሶስት ምስል የሆነና የአንዱ አንግል ልኬት ከ90° የበለጠ እና ከ180° ያነሰ ልኬት ያለው ነው።

ሀ. ሹል አንግል ሐ.ዝርጥ አንግል

ለ. ማዕዘናዊ አንግል መ.ጥምዝ አንግል

22. የሁለት አንግሎች ልኬት ድምር 180° ከሆነ፤ ሁለቱ አንግሎች --------- ይባላሉ።

ሀ. ቀጤ አሟይ ሐ.ዝርግ አሟይ

ለ. ጀርባ ጀርብ አንግል መ.ጉርብት አንግሎች

23. -------- መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው ።

ሀ. ሙከራ በመስራት ሐ.ከበይነ መረብ

ለ. ጥያቄ በመጠየቅ መ.ሁሉም መልስ ናቸው

በለሚ ኩራ ክ/ከተማ ትምህርት ጽ/ቤት የ6ኛ ክፍል የሒሳብ ሞዴል ፈተና /ግንቦት 2015 ዓ.ም

24. አንድ ቤተሰብ የወር ገቢው 6000 ብር ነው። ከዚህ ውስጥ 18° የሚሆነውን ለመብራት ቢያውል ፤በብር መጠን ሲገለፅ------- ነው።
ሀ. 300 ብር ሐ.200 ብር
ለ. 500 ብር መ.100 ብር

25. አንግል <ሀ እና <ለ ቀጤ አሚይ አንግሎች ናቸው፤ <ሀ =34° ቢሆን <ለ --------ይሆናል።
ሀ. 56° ሐ.30°
ለ. 54° መ.60°

26. ------- ምንም መለያያ ነጥብ የሌለው እና ባለሶስት ገፅ የሆነ የጂኦሜትሪ ጠጣር ምስል ነው ።
ሀ. ጎነ ሶስታዊ ፒራሚድ ሐ. ፕሪዝም
ለ. ሲሊንደር መ.ካሬ ፕሪዝም

ትእዛዝ 2፦ ከዚህ በታች የተሰጠውን በአንድ ቤተሰብ የተመዘገበ የእድሜ መጠንን በመመልከት ከ27 -30 ያሉትን ጥያቄዎች መልሱ

የቤተሰብ ስም	ሰለሞን	ማርታ	ግርማ	አስፋው	አልማዝ	ሄኖክ
ዕድሜ	48	12	34	60	56	60

27. የቤተሰቡ አማካይ እድሜ ---------- ይሆናል።
ሀ. 48 ሐ.55
ለ. 38 መ.45

28. ሚዲያኑ ስንት ነው?
ሀ. 60 ሐ.52
ለ. 55 መ.41

29. በተሰጠው መረጃ ውስጥ -------- ሞድ አለው።
ሀ. ባለ ሁለት ሐ.ሞድ የለሽ
ለ. ባለ ሶስት መ.ባለ አንድ

30. ከተሰጠው መረጃ ውስጥ ሬንጁ ስንት ነው?
ሀ. 48 ሐ.34
ለ. 12 መ.60